# እግዚአብሔር አብወእም፡
# እንኳን፡
# ልጃቸው ኢየሱስ መሲሕ፡
# በግርማ መለኮቱ ተገልጾ የታየበትን፡
# የደብረ ታቦርን በዓል፥
# ዘንድሮም፡ በ፳፻፰ተኛው (በኹለት ሺ ስምንተኛው)
# ዓመተ ምሕረት፡
# በያለንበት፡ በደኅና አድርሰው፡
# በሰላም ለማክበር አበቁን!

+ + +

## የደብረ ታቦር (ቡሔ) በዓል።

ለእኛ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ከዓበይት በዓሎቻችን፡ አንዱ የኾነው፡ በዓለ ደብረ ታቦር የሚውለው፡ በነሓሴ ፲፫ ቀን በመኾኑ፡ ለጾመ ፍልሰታ ሱባዔ፡ ልዩ ምዕራፍ ኾኖ፡ በታላቅ መንፈሳዊ ተመስጦና ማኅሌት ይከበራል።

ይህ በዓል፡ ከመድኀኒታችን፡ ከእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም፡ በሰውነት የተወለደው፡ ሰላማችን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ በዐጸደ ሥጋ፡ ዐብረውት ከነበሩት ደቀ መዛሙርቱ መካከል፡ ጴጥሮስንና ያዕቆብን፥ ወንድሙንም ዮሓንስን፥ በዐጸደ ነፍስ ካሉት ባለሟሎቹ ደግሞ፡ ሙሴንና ኤልያስን፡ ከኢየሩሳሌም በስተምሥራቅ በሚገኘው፡ "ታቦር" በተባለው፡ የወይራ ዛፍ ተራራ ላይ አምጥቶ፡ የባሕርይ አምላክነቱን በመግለጥ፡ ታማኞች አገልጋዮቹ፡ ሊያዩ የተመኙትን፡ እንዲያዩ፥ ሊሰሙ የተመኙትንም፡ እንዲሰሙ ያደረገበት ቸርነቱና ኃይሉ የሚዘከርበት ነው።

ይህንም፡ እርሱ፡ ጌታችንና ሰላማችን፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ ለሕዝቡ፡ በምሳሌ ያስተምራቸው የነበረው፡ ነቢዩ ኢሳይያስ፡ **"እስመ እንዘ ይሬእዩ፡ ኢይሬእዩ። ወእንዘ ይሰምዑ፡ ኢይሰምዑ፤ ወኢይሌብዉ።"**

ማለትም፡ "እያዩ፡ ስለማያዩ፥ እየሰሙም፡ ስለማይሰሙ፤ ስለማያስተውሉም" ወገኖች፡ የተናገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ መኾኑን፡ ለደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ፡ መልስ በመስጠት ያስረዳቸው ቃሉ፡ በሥርዓተ ቅዳሴ ጸሎት ላይ፡ ዘወትር ይወሳል።

ይህም፡ "ወለክሙሰ፡ ብፁዓት አዕይንቲክሙ፡ እስመ ይሬእያ፤ ወዕዘኒክሙ፡ እስመ ይሰምዓ። አማን እብለክሙ! ከመ ብዙኃን ነቢያት ወጻድቃን፡ ፈተዉ ይርአዩ፡ ዘትሬእዩ፤ ወኢርእዩ። ወፈተዉ ይስምዑ፡ አንትሙ ዘትሰምዑ፤ ወኢሰምዑ።"

ማለትም፡ "የእናንተ ግን፡ ዓይኖቻችሁ፡ እነሆ ስለሚያዩ፥ ጆሮዎቻችሁም ስለሚሰሙ፡ ብፁዓት ናቸው። እውነት እላችኋለሁ! ብዙዎች ነቢያትና እውነተኞች፡ እናንተ፡ ዛሬ የምታዩትን፡ ሊያዩ፡ እጅግ ፈልገው ነበር፤ ነገር ግን፡ አላዩም። እናንተ፡ ዛሬ የምትሰሙትንም፡ ሊሰሙ፡ እጅግ ፈልገው ነበር፤ ነገር ግን፡ አልሰሙም።" ሲል፡ ለደቀ መዛሙርቱ የተናገረው ነው። (ማቴ. ፲፫፥ ፲፫-፲፯።)

በዚያ የታቦር ተራራ ላይ፡ የታየውንም ተአምራት እንዲህ የሚለው ዜና፡ አጠቃልሎ ይገልጸዋል፦

"ነሥኦሙ እግዚእ ኢየሱስ፡ ለጴጥሮስ፥ ወለያዕቆብ፥ ወለዮሐንስ፤ ወዐርገ ደብረ፡ ከመ ይጸሊ። ወእንዘ ይጼሊ፡ ተወለጠ ርእየተ ገጹ፤ ወአልባሲሁኒ ፃዕደወ፤ ወበረቀ ከመ መብረቅ።

"ወናሁ መጽኡ ክልኤቱ እደው፤ ወይትናገሩ ምስሌሁ፤ እሉ እሙንቱ፡ ሙሴ፥ ወኤልያስ። እሉ አስተርአዩ በስብሓት፤ ወነገሩ ስብሓቲሁ፡ ዘሀለዎ ይኩን በኢየሩሳሌም፤ ወፀአቶሂ።

"ረከበ ጴጥሮስሃ፥ ወእለ ምስሌሁ፡ ክቡዳን አዕይንቲሆሙ በድቃስ፤ ወነቂሖሙ፡ ርእዩ ስብሓቲሁ፤ ወእደውኒ ክልኤቱ፡ እለ ይቀውሙ ምስሌሁ።

"ወእምዝ ሶበ ፈቀዱ ይትሌለዩ እምኔሁ፡ ይቤሎ ጴጥሮስ፡ ለእግዚእ ኢየሱስ፦ 'ሊቅ! ይኄይሰነ ንንበር ዝየ፤ ወንግበር ሠለስተ ሰቃልወ፤ አሓደ፡ ለከ፤ ወአሓደ፡ ለሙሴ፥ ወአሓደ፡ ለኤልያስ።' ወኢየአምር ዘይብል።

"ወዘንተ ብሂሎ፡ ጸለሎሙ ደመና። ወፈርሁ፡ ሶበ ቦኡ ውስተ ደመና። ወመጽአ ቃል፡ እምውስተ ደመና፤ ዘይብል፦ 'ዝንቱ ውእቱ ወልድየ፡ ዘኅረይኩ! ወሎቱ ስምዕዎ!'

"ወመጺአ ቃል፡ ተረክበ እግዚእ ኢየሱስ ባሕቲቱ። ወእሙንቱሰ፡ አርመሙ፤ ወኢነገሩ፣ ወኢለመኑሂ፡ ዘርእዩ፥ ወዘሰምዑ ውእተ አሚረ።"

ማለትም፡ "አምላካችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ጴጥሮስንና ዮሓንስን፥ ያዕቆብንም ይዞ፡ ሊጸልይ፡ ወደተራራ ወጣ። ሲጸልይም፡ የፊቱ መልክ ተለወጠ፤ ልብሱም፡ ተብለጨለጨ፤ እንደመብረቅም፡ አብረቀረቀ!

"እነሆም፡ ኹለት ሰዎች፡ መጡ። ከእርሱም ጋር ይነጋገሩ ጀመር። እነርሱም፡ ሙሴና ኤልያስ ናቸው፤ በክብርም ተገልጠው ታዩ። የእርሱንም፡ ወደኢየሩሳሌም መውጣት፥ በዚያም ስለሚኾነው ክብሩ ኹሉ ተናገሩ።

"ነገር ግን፡ ጴጥሮስንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን፡ ዓይኖቻቸው፡ በእንቅልፍ ከብደውባቸው አገኛቸው፤ ባነቃቸው ጊዜ፡ ክብሩንና ከእርሱ ጋር ዐብረው የቆሙ፡ ኹለት ሰዎችን አዩ።

"ከዚህ በኋላ፡ ከእርሱ ሊለዩ ሲፈልጉ፡ ጴጥሮስ፡ ለጌታችን ኢየሱስ፡ እንዲህ ይለው ጀመር፡- 'መምህር ሆይ! በእዚህ መኖር፡ ለእኛ ይሻለናልና፡ እባክህ! አንድ፡ ለአንተ፤ አንድ፡ ለሙሴ፤ አንድ፡ ለኤልያስ፡ ሦስት ዳሶችን እንሥራ!' የሚናገረውን አያውቅም ነበር።

"ይህን እየተናገረ ሳለ፡ ደመና መጣና ጋረዳቸው። ወደደመናውም ሲገቡ፡ ፈሩ። ከደመናውም ውስጥ፡ እንዲህ የሚል ቃል መጣ፡- 'ይህ፡ የመረጥሁት ልጄ ነው! እርሱን ስሙት!'

"ይህ ቃል መጥቶ እንደተሰማ፡ ጌታችን ኢየሱስ፡ ብቻውን ኾኖ ተገኘ። እነርሱም፡ ዝም አሉ፤ ስላዩትም፥ ስለሰሙትም፡ ስለዚህ ትንግርት፡ በዚያች ወራት፡ ምንም ነገር፡ ለማንም፡ ከቶ አልተናገሩም።" (ሉቃ. ፱፥ ፳፰-፴፮።)

## ቡሔ።

የደብረ ታቦር በዓል፡ በሕዝባዊ ዘይቤ፡ "ቡሔ" ተብሎ ይከበራል። በበዓሉ ዋዜማ፡ በየቤቱ፡ ችቦ ከበራ በኋላ፡ ከሠርክ ጀምሮ፡ በምሽቱ ጊዜ፡ ወጣቶች ወንዶች ልጆች፡ በየሠፈራቸው፡ በቡድን፡ በቡድን እየኾኑና በትር በትራቸውን ይዘው፥ ጅራፍ ገምደው እያጮሁ፥ ለበዓሉ የተለመደውንም፡- *"ቡሔ በሉ! ሆ! ልጆች ኹሉ! ሆ! እዚያ ማዶ፡ ጭስ ይጨሳል! አጋፋሪ ይደግሳል! ያንን ድግሥ፡ ውጬ ውጬ! በድንክ አልጋ፡ ተገልብጬ! ያች ድንክ፡ ዓመለኛ! አላንድ ሰው አታስተኛ!"* የሚለውን የጭፈራ ሆታ፡ በመቀባበል እያሰሙ፡ "እንኳን አደረሳችሁ!" ለማለት፡ በመንደራቸው መኖሪያ ቤቶች ኹሉ ይዘዋወራሉ።

በየገቡበት ቤትም፡ ዙሪያውን ከብበው፥ በበትራቸው፡ ወለሉን እየደቁና ከአንዱ የሆታ አውራጅ ጓደኛቸው፡- *"ሆያ ሆዬ! ሆ! የኔ ጌታ! የሰጠኝ ሙክት! መስከረም ጠባ፡ ያንን ሳነክት! ...ሆያ ሆዬ! ሆ! የእኔ እመቤት! የፈተለችው! የሸረሪት ድር፡ አስመሰለችው! ያንንም ኩታ፡ ማርያም ሠራችው! ለዚያች ለማርያም እዘኑላት! ባመት ከመንፈቅ፡ አለቀላት!"* የሚለውን፡ የሆታ ዜማ እየተቀባበሉ፡ የቤቱን አባወራና እመቤት ያሞግሳሉ። ባለቤቶቹም፡ "እንኳን፡ ዐብሮ አደረሰን! ደግሞም፡ ለከርሞ (ለሚመጣው ዓመት)፡ እንዲሁ፡ በሰላም ያድርሰን! የዘንድሮውም፡ የቡሔ ዳቢችሁ፡ ይኸውላችሁ!" ብለው፡ ትኵሱን፡ ሙልሙል የቡሔ ኅብስት አበርክተውላቸውና መርቀዋቸው፡ ያሰናብቷቸዋል። ልጆቹም፡ ያንን ምርቃትና የቡሔ ዳቦ ተቀብለው፡ *"ዓመት ዐውደ-ዓመት፡ ድገመን ዓመት! ድገመን ዓመት! የጌታዬ ቤት! ድገመን ዓመት! ድገመን ዓመት! የእመቤቴ ቤት! ድገመን ዓመት! ድገመን ዓመት! እንደዚሁ እንዳላችሁ! ሆ! አይለያችሁ!"* እያሉ፡ መልካም ምኞታቸውን በመግለጽ፡ እጅ እየነሡ ይወጣሉ።

"ቡሔ"፡ በኢትዮጵያኛ፡ "ቡሔዬ"፥ ብርሃኔ፥ መብራቴ ማለት ነው። በደብረ ታቦር፡ ማለትም፡ በዚያ፡ በታቦር ተራራ ላይ፡ እንደመብረቅ የብልጭታ ብርሃን፡ "ቧ" ብሎ የተገለጠውን፡ የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕን፡ የፊቱን ጸዳል፥ የልብሱንም፡ እንደበረዶ ነጭ መኾን ያስረዳል፤ የችቦው መብራት ምሳሌ፡ ይህ ነው።

ደግሞም፡ በኢትዮጵያኛ፡ "ለከት" ማለት፡ "ታናሽና ሞላላ፡ የሊጥ መፈተኛ፥ ጢብኛ፥ የዳቦ እንጎቻ" ማለት ሲኾን፡ እረኞች፡ በዚሁ፡ በቡሔ ዋዜማ ሲጨፍሩ፡ "አክስቴ ቤት፣ አለኝ ለከት!" ከሚሉት ሙልሙል የተነሣ፡ "ቡሔ" በግእዝ፡ "ብሖእየ"፡ ማለትም፡ "ብሖዬ" ተብሎ ስለሚተረጎም፥ ለከት፣ ወይም፡ ዳቦ ኾኖ ሊጋገር፡ የሚቦካ ሊጥም፡ በግእዝ፡ "ብሒእ" ስለሚባል፡ ለደብረ ታቦር በዓል ዕለት፡ ተቦክቶ የሚጋገረውን ኅብስት ያሳያል፤ ስለዚህ፡ "የቡሔ ዳቦ" የሚባለው ኅብስት፡ ባሕርየ መለኮቱ፡ በደብረ ታቦር የተገለጠው፡ የአምላካችን የኢየሱስ መሲሕ ምሳሌ መኾኑን፡ ማስተዋል ይገባል። (የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤ ደ.ተ.ወ. ገጽ. ፪፷፩።)

በዘመነ ብሉይ፡ ሙሴ፡ ከባለሟልነቱ የተነሣ፡ አምላኩን እግዚአብሔርን፡- **"አርእየኒኬ ስብሓቲከ!"**

ማለትም፡ **"እባክህ! ፊትህን (ክብርህን) አሳየኝ!"** ባለው ጊዜ፡ እግዚአብሔር ለሙሴ፡ የሰጠው የተስፋ መልስ፡-

**"ርእዮተ ገጽየሰ፡ እስመ አልቦ ዘይሬኢ ገጽየ፤ ወየሓዩ። ወናሁ ትመጽእ ጊዜ፡ እንተ ባቲ ትሬእየኒ!"**

ማለትም፡ **"ሰው፡ አይቶኝ አይድንምና፡ ዛሬ፡ ፊቴን ማየት አይቻልህም፤ የምታይባት ጊዜ ግን ትመጣለች።"** የሚል ነበረ። (ዘጸአ. ፴፫፥ ፲፰-፳፫። ማር. ፱፥ ፪-፰።)

ያ፡ የተስፋ ቃል ተፈጽሞለት፡ ሙሴ፡ በዚያ ጥያቄው ጊዜ፡ በግርማ መለኮትነቱ ባሕርይና አካል፡ ሊያየው ያልቻለውን፥ በኋላ ዘመንም፡ **"ይህ ሥጋዬ ነው፤ ብሉት!"** ብሎ፡ ራሱን፡ ኅብስት አድርጎ ያቀረበውን፡ እግዚአብሔር ወልድን፡ በታቦር ተራራ ላይ፡ በሰውነት አካልና ባሕርይ ገዝፎ፡ ሊያየው ችሏል።

የቤተ ክህነታችን ምሁራን፡ በዚህ ረገድ፡ **"ገራህተ ሙሴ አንቲ ነሽ!"** ማለትም፡ **"የሙሴ ማሳው፡ አንቺ ነሽ!"** በሚለው በማግሰኞው የውዳሴ ማርያም ትርጓሜያቸው፡ የሚሰጡትን ሓተታ፡ እዚህ ላይ ማውሳቱ፡ አግባብ ይኾናል።

ይህም፡ እንዲህ የሚል ነው፡- *"ሙሴ፡ ከባለሟልነቱ የተነሣ፡ [*ቃሉን እያሰማ የሚያነጋግረውን እግዚአብሔርን፡] *'ባይህ እወድዳለሁ!' አለው።*

*"እግዚአብሔርም፡ 'የእኔን ፊት አይቶ፡ አንድ ሰዓት መቆም፥ መቆየትም የሚቻለው የለም!' አለው።*

*"ሙሴም፡ 'ካላየሁህማ፡ ለምን፡ ባለሟልህ ተባልሁ?' አለው።*

*"እግዚአብሔርም፡ 'ፊቴን፡ ከኋላዬ እንጂ፡ ከፊት ለፊት አላሳይህም!'* [ይህም ማለት፡] *ዘር ካልወደቀባት ምድር፡ የበቀለ ስንዴን፡ አምጥተህ ብትሠዋልኝ፡ እታይሃለሁ!' አለው።*

*"'ሙሴ' ማለት፡ 'የዋህ' ማለት ነው። ለጊዜው፡ በራእይ ሲባክን አድሩዋል፤ ፍጻሜው ግን፡* በ[ሰብኣዊ] *ዘር ከተወለደች፡ ከድንግል፡ ያለ[ሰብኣዊ] ዘር ተወልጄ፡ ኋላ፡ በደብረ ታቦር፡ መሥዋዕት ኾኜ በምቀርብበት ጊዜ፡ እታይሃለሁ!' ሲል ነው። መምህር ኤስድሮስ ግን፡* [ሙሴ፡ በዐፈር የተሞላ] *የብረት መደብ አሥርቶ፡ ውኃ እያጠጣ፡ አሸክሞ፡ ዐርባ ዘመን ዙርዋል!' ብለዋል።"*

እንግዴህ ዛሬ፡ በደብረ ታቦር ዕለተ በዓል ዋዜማ፡ ማለትም፡ በቡሔ ምሽት፡ "የቡሔ ዳቦ" ተብሎ፡ ለሕፃናትና ለብላቴኖች፥ ለወጣቶችና ለጐልማሶችም የሚበረከተው ኅብስት፡ የዚህ ምሳሌ ነው።

የወንዶቹ ልጆች፡ የሆታ ጭፈራ የሚያዘክረው፡ ከደስታውና ከድንጋጤው የተነሣ፡ *"የሚያደርገውን አያውቅም ነበር!"* የተባለውን፡ የቅዱስ ጴጥሮስንና የቀሩትን፡ የኹለቱን ሐዋርያት አድራጎት ሲኾን፥ የችቦው መብራት፥ ጅራፉና ጩኸቱ ደግሞ፡ በዚያን ተራራ ላይ፡ ከጋረዳቸው ደመና ውስጥ፡ ብርሃነ መለኮቱን ለመግለጽ፡ ከታየው መብረቃዊ የብልጭልጭታ ብርሃን ጋር ለተሰማው፡ ነጐድጓዳዊ የመለኮት ድምፅ፥ በተለይም፡ የሰላማችን የኢየሱስ ክርስቶስን መገረፍ የሚያስታውስ ምሳሌ ነው።

## የደብረ ታቦር/የቡሔ በዓል፡
## ጸሎተ-ቅዳሴ ምንባባትና ምስባክ።

**ምንባቦች፡-**

፩ኛ፡ ዕብ. ምዕ. ፲፩፥ ቍ. ፳፫-፴፩፤
፪ኛ፡ ፪ጴጥ. ምዕ. ፩፥ ቍ. ፲፮-፳፩፤
፫ኛ፡ የሐዋ. ምዕ. ፯፥ ቍ. ፵፬-፶።

**ምስባክ፡-**

| | |
|---|---|
| ታቦር፥ ወአርሞንዔም፡ በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ፤ | ታቦርና አርሞንዔም፡ በስምህ ይደሰታሉ፤ |
| ወይሴብሑ ለስምከ፤ | ስምህንም፡ ያመሰግናሉ፤ |
| መዝራዕትከ፡ ምስለ ኃይል። | ክንድህ፡ ከኃይልህ ጋር ነው። |

**ወንጌል፡-** ሉቃ. ምዕ. ፱፥ ቍ. ፲፰-፴፮።

\+ + +